# የቤተክርስቲያን አመራር
# (Church Government)

**Bild 1**

1 slide 44 is repeated?
Ayele Nigatu; 2016-12-28

2

# በቤተክርስቲያናችን የእረኛ ጉዳይ የሚመለከት የተደረጉ እርምጃዎች

- በ2009 (እ. ኤ. አ.) የእረኛ አፈላላጊ ጊዜያዊ ኮሚቴ/ቡድን በሽማግሌዎች አገልግሎት ተቋቋመ::
- የእረኛ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት:
  - ወንድም ንጉሱ ጉሌ - የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወክሎ
  - ወንድም አልዓዛር ገዳሙ
  - ወንድም አየለ ንጋቱ
  - እህት ምንትዋብ ወንድሙ
  - እህት ታደለች ዋናና
  - ወንድም ዮሐንስ ዓሥራት
- የተቀበለው ተልእኮ
  - ”በቀድሞ የቤተክርስቲያኒቱ ደንብ መሰረት በእረኝነት ሊያገለግል የሚችለው ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኛ ምን መሆን እንዳለበት አጥንቶ ለሽማግሌዎች አገልግሎት አቅርቦ እንዲወያይ ከዚያም እረኛ በማስመረጥ እንዲያግዝ”
- የሄደበት አካሄድ
  - ከ 2009-2013 ለ4 ዓመታት ለብቻው （27 ስብሰባዎች）
  - ከ 2013-2015 ለ1 ዓመት ተኩል ከሽማግሌዎች አገልግሎት ጋር （24 ስብሰባዎች）
  - በ2015 1 ዓመት ያህል ከቃል አገልጋዮችና የአገልግሎት ቡድን መሪዎች ጋር （6 ስብሰባዎች）
  - በ2016 ከጉባኤው ጋር (April 23) (1 ስብሰባ)
  - በ2016 ከጉባኤው ጋር (May 21 / April 05)



”እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ
ልበ ሰፊዎች ነበሩና።
ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው
ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ
ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።”
(ሐዋ. 17:11)

# የጥናቱ ህዳር

- መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ምንጭ ያደረገ
- እትሞች
  - የ1954 የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ
  - እንደ አስፈላጊነቱ የተለያዩ የአማርኛና የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትሞችን
- የቤ/ክንን አመራር/አስተዳደርን (governance)
- በአዲስ ኪዳን ላይ በተጻፉ ክፍሎች ላይ
- በጊዜ በተገደበ

# ጥናቱ የተካሄደበት መንገድ

- የቃሉን ቀጥተኛ ትርጉም በክፍሉ ይዘት ላይ በመመርኮዝ
- ከዚህ በፊት የነበረንን የግል መረዳት / እውቀት ወደጎን በመተው
- የሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት እምነት/ አሠራር በምንም መልኩ ማስተያያ ባለማድረግ
- በቃሉ ከተጻፈው ሃሳብ ጋር የሚቃረኑ አነጋገሮችንና አመለካከቶችን በማገረም
- የሐዋርያት ዘመን ቤተክርስቲያንን ሞዴል በማድረግ

# ከዚህ ፕሮግራም ምን እንጠብቅ？

# የእኛ መነሻ እና የእግዚአብሔር ሰፊ ሃሳብ

| እኛ የተነሳንበት | እ/ር በቃሉ ያመራን |
|---|---|
| አንድ እረኛ /እረኝነት አገልግሎት | የአምስቱ አገልግሎት ስጦታዎች አስፈላጊነት |
| በቤተክርስቲያን ደንብ መሠረት | ** የቃሉ ልዩ መሠረት |
| እረኛ ማፈላለግ | የእኛና የሕዝቡ ለእ/ር መገኘት |

"እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና።

ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው

ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።"

**(ሐዋ. 17:11)**

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡-

<u>መጻሕፍትንና</u>

<u>የእግዚአብሔርን ኃይል</u>

አታውቁምና ትስታላችሁ።

ማቴ 22:29

# የቤ/ክ አመራር ለምን? እንዴት?

# ለምን ?

- **የቤ/ክ አመራርን አስመልክቶ ያሉ ችግሮች/ ውዝግብች**
  - በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ብዙ የአመራር ልዩነቶች መኖራቸው
  - የመረዳት ልዩነቶችና በአሰራርም ላይ የአገልግሎት ሚናን ካለመለየት የሚመነጩ ግጭቶች
  - ስለቤ/ክ አመራርና ስለሌሎችም ጉዳዮች ከእግ/ር ቃል ጋር የሚጋጩ ብዙ እውነት-መሳይ አባባሎች/ግምቶች/ድምዳሜዎች (myths) ስላሉ

# ስለዚህ ?

- መጽሐፍ ቅዱስን ብቸኛ መመሪያ የማድረግ አስፈላጊነት Vs የእኛ ወይንም የሌሎች ቤ/ክያናት ልምምድ
- የመጀመሪያዪቱ ዘመን የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ለአሁን ዘመን ቤተክርስቲያን የተሻለ ሞዴል/ ምሳሌነት

# የሐዋርያት ቤተክርስቲያን የተሻለ ሞዴልነት

- ቤተ ክርስቲያን እውን የሆነችው በአዲስ ኪዳን ስለሆነ
- ከመጀመሪያይቱ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በኋላ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች እየተሸረሸሩ በመሄዳቸው
- እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለማግኘት
- ወደ መጀመሪያ የመመለስ አስፈላጊነት

# የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ሞዴልነት (የቀጠለ)

- መጽሐፍ ቅዱስን ለመጻፍ ጌታ ባመናቸው ሐዋርያት የተመሰረተች በመሆኗ
- የበጉ ሐዋርያት እራሳቸው የመሯትና ያስተዳደሯት ቤተክርስቲያን ስለሆነች
- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሳኤ ለማወጅ አደራ የተሰጣትና የተወጣች በመሆኗ

# የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ሞዴልነት (የቀጠለ)

- በእግዚአብሔር ቃል ትምህርትና ታማኝነት ሞዴል
- በታላቅ ሃይል እግዚአብሔር ምልክትና ድንቅ በማድረግ ስለጸጋ ቃሉ የመሰከረባት ቤተክርስቲያን ስለሆነች
- በሐዋርያት ላይ ይታይ የነበረው ራስን ፈጽሞ ለጌታ መስጠትና ራሳቸውን የካዱ ሰዎች መሆናቸው

# ወደ መረዳት አንድነት የመምጣት አስፈላጊነት

- “ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ <u>በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ</u> እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ።” (1ቆሮ 1:10)

- “በክርስቶስም አንዳች ምክር ቢሆን፥ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፥ የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፥ ምሕረትና ርኅራኄ ቢሆኑ፥ ደስታዬን ፈጽሙልኝ፤ <u>በአንድ አሳብ ተስማሙ”</u> (ፊልጵ 2:1-2)

# መሠረተ ሃሳቦች

- የእግዚአብሔር ቃልና አተረጓጎሙ
- የቤተክርስቲያን ማን/ምንነት



# የእግዚአብሔር ቃል ማዕከላዊነት

- ልምድንና ወግን ከእግዚአብሔር ቃል የማስቀደም ችግር ልንጠነቀቀው የሚገባ ችግር ነው!

(ማር 7፣8,13) የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ ጽዋን ማድጋንም እንደ ማጠብ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ፥ ይህንም የመሰለ ብዙ ሌላ ነገር ታደርጋላችሁ።...ባስተላለፋችሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፤ እንደዚሁም ይህን የሚመስል ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ።

- የክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስነት/ ማዕከላዊነቱ ዕውን የሚሆነው የእግዚአብሔር ቃል ማዕከላዊ ሲሆን ነው

# የእግዚአብሔር ቃል ምንነትና ሥልጣን

- መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው ቅዱሳን ሰዎች የጻፉት የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት (ኢንስፓየርድ የሆነ) መሆኑን መቀበል ይገባናል:: (2ኛ ጢሞ 3፥16-17፣ 2ኛ የጴጥ 1፥21)
- 2ኛ ጢሞ 3:16-17 የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።

# የእግዚአብሔር ቃል አተረጓጎም

- በተባለበት መንገድ መቀበል
  - ሉቃ 8:18 "እንዴት እንድትሰሙ ተጠበቁ"!
- 2ኛ ጴጥ 1:16-21

የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ። ከገናናው ክብር። በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና፤ እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን። ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፥ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ። ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።

# የእግዚአብሔር ቃል አተረጓጎም (የቀጠለ)

- መጽሐፍ ቅዱስ ዘመንና ሁኔታን የተመለከተ አቀራረብ/ይዘት ቢኖረውም የሚያስተላልፈው መልእክት ሁሉ ግን በጊዜና በሁኔታ ወይንም በባሕል የማይወሰን ነው!
  - እሴቶችና እውነቶች ከዘመንና ከባሕል ጋር አይቀያየሩም!
  - አሰራር ልዩ ልዩ ነው የቃሉ መልእክት ግን አንድ ነው!
  - ሐዋሪያው ጳውሎስ ራሱ ሌሎቹን ሰዎች ለመጥቀም በሌሎች ሰዎች ባህል ሂዶ ነበር

# የእግዚአብሔር ቃል አተረጓጎም (የቀጠለ)

የመንፈስ ቅዱስን ገላጭነትና አስተማሪነት መተማመን ይገባናል

- ”1ኛ ዮሐ 2፣27 እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፥ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ፥ እናንተንም እንዳስተማራችሁ፥ በእርሱ ኑሩ።”
- ”ዮሐ 14፣26_27 አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።”

# የእግዚአብሔር ቃል አተገኳጎም

- ስንተረጉም በቃሉ ከተጻፈው አልፈን እንዳንሄድ መጠንቀቅ
- አስተምሮአችንንን በልምምዶቻችን ላይ አለመመስረት
- በአብያተክርስቲያናት ልምምዶች ቃሉን ለመተርጎምና አለመሞከር
- አውደ ምንባባዊ አተረኳጎም
- በግልጽ (ኤክስፐሊሲት) የሰፈሩና በምልከታ (ኢንፈረንስ) የሚገባን
- የምሳሌያዊ/ንጽጽራዊ (Alagorical) አተረኳጎም መሠረታዊ አቋም (ዶክትሪናል) ደረጃ መምጣት የለበትም

# የእግዚአብሔር ቃል አተገጓጎም

- ቃሉ ለሁሉ በሚገባ ደረጃ የተጻፈ ነው
- ቃሉ ራሱን ይተረጉማል::
- ትህትናና እውነተኛነት - ቃሉን በተጻፈበት መልክና ደረጃ መረዳት
- ዲደክቲቭና ኢንደክቲቭ
- “የእኔ አቋም” “የእኛ አቋም” ” የሚሉት አባባሎች ቃሉን እንዳናጠናና እንዳንረዳ እንቅፋት ይሆናሉ
- “እንደ ቤርያ ሰዎች ቃሉን መመልከት”

# ከጉባኤው ጥያቄዎች ?

# የመወያያ ጥያቄዎች 1

- ኤፌሶን ፬ ላይ የተጠቀሱ አምስት አገልግሎቶች ሲሆኑ በዚህ ዘመን በአንዱ ላይ ብቻ መተኮሩ ልክ ነው ወይ? ይሄ የሆነውስ ለምን ይመስላችኋል?
- እንደቤርያ ሰዎች ቃሉን ማጥናት ስንል እንዴት ባለ ልብ ሆነን ማጥናትን ይጠይቀል? ምን ምን አይነት ነገሮችን ያጠቃልላል?
- የእግዚአብሔር ቃል የበላይ ባለስልጣን ነው የሚለውን  አባባል እንዴት እንረዳዋለን  ይሄስ አባባል በመጽሐፍ ቅዱስ ይደግፈዋልን?
- በበጉ ሐዋርያት ይመሩዋት የነበረችይቱን የመጀመሪያይቱን ዘመን በምን በምን ትታወቅ ነበረ?
- ሐዋ. ሥ.ም. ፳ ላይ የምናየው ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ልኮ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን አስጠራ የሚለውን ነው፥ ከዚህ አባባል ስለመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን አመራር ምን እናስተውላለን?



”እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ
<u>ልበ ሰፊዎች</u> ነበሩና።
ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው
<u>ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ</u>
ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።”
**(ሐዋ. 17:11)**





"በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን፥ አቁማዳው ይፈነዳል፥ የወይን ጠጁም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል፤ ነገር ግን አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ያኖረዋል፥ ሁለቱም ይጠባበቃሉ።"

(ማቴ. 9፥17)

# ቤተክርስቲያን

## ”ኤክሌሺያ”

ትርጉሙም (”ኤክ” = ”ከ”…”ወደ”… ”መውጣት” እና ”ካሊኦ” = ”መጠራት” በሚሉ ስርወ-ቃሎች በመነሳት) ከአለም ወደ እግዚአብሔር የተጠሩ ሰዎች ማለት ነው፤ የሚያመለክተውም እግዚአብሔር ከአለም ወደ ዘለአለም መንግሥቱ የጠራቸው አማኞችን ነው።

ማቴ 16:18 ”እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን (”ኤክሌሺያ”) እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።”

# ቤተክርስቲያን (የቀጠለ)

- የክርስቶስ አካል

  ኤፌ 4:4,5 "በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።"

- አጥቢያ ቤተክርስቲያን

  ሐዋ 9:31 "በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።"

# የክርስቶስ አካል / አለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን

- ”በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።” ኤፌ 4፥4-5
- ”ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤” ኤፌ 5፥25
- ”እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው።” ቆላ 1፥18

# አለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን (የቀጠለ)

"መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ።"

ራእ 5፥9-10

# አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

- "በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ("ኤክሌሽያ")..." 2ኛ ቆሮ 1፥1
- "በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ።" ራእ 2፥1
- "በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።" ሐዋ 9፥31
- "በቤታቸውም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከእስያ ለክርስቶስ በኵራት ለሆነው ለምወደው ለአጤኔጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ።" ሮሜ 16፥5
- "በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት፥ የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት፤" 1ኛ ቆሮ 1፥2

# ቤተመቅደስ እና ቤተ ክርስቲያን

## በአዲስ ኪዳን “ቤተመቅደስ” የአማኞችን ሰውነት/ አካል/ ሥጋ ያመለክታል!

- ”ኢየሱስም መልሶ፡-ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው።” ዮሐ 2፥19 (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ራሱ ሰውነት ሲናገር ይህን አለ::)
- ”ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።”1ኛ ቆሮ 6፥19-20
- ”ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል፡- በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።” 2ኛ ቆሮ 6፥16
- ”የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።”1ኛ ቆሮ 3፥16-17

# የቤተ ክርስቲያን አመራር በሐዋርያት ዘመን

# ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ናት!

- "እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ <u>ቤተ ክርስቲያኔን</u> እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።"ማቴ 16፥18
  - "በገዛ ደሙ የዋጃትን <u>የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን</u> ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።"ሐዋ 20፥28
  - "በቆሮንቶስ ላለች **ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን**፤"2ኛ ቆሮ 1፥1
  - "እኔ ደግሞ ብዙዎቹ ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር ሰውን ሁሉ ደስ እንደማሰኝ፥ ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች **ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም** ማሰናከያ አትሁኑ።"1ኛ ቆሮ 10፥32-33

# ቤተ ክርስቲያን ራስ በሆነው በክርስቶስ ትመራለች

- "እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ ከሙታንም በኵር ነው።" ቆላስ. 1፥18
- "ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው። እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት።" ኤፌ 1፥22-23
- "...ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና።... ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።" ኤፌ 5፥23, 31-32
- "የእረኞችም አለቃ (Chief shepherd') በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ።" 1ኛ ጴጥ 5፥4

# የክርስቶስ አመራር በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነው

- “እርሱ ራሱ ያከብረኛል” (እውቅና) ዮሐ 16፥14
- “እኔ ብሄድ ይሻላል…“ (ምትክ/ውክልና) ዮሐ 16፥7
- “እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ። በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ።“ ሐዋ 13፥2,4;14፥14
- “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።“ ሐዋ 20፥28
- “ለጣዖት ከተሠዋ፥ ከደምም፥ ከታነቀም፥ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና፤ ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ። ጤና ይስጣችሁ።“ ሐዋ 15፥28-29

# አመራር በአምስቱ አገልግሎቶች በኩል

"ስለዚህ፡- ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ ይላል። ወደ ምድር ታችኛ ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ፥ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው? ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው። እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።" ኤፌ. 4፥8-13

"እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም፥ አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል።" ፩ኛ ቆሮ ፲፪፥28

# አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች በቤተክርስቲያን አመራር

“እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ። እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኰል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም፥” ኤፌ 4፥11-14

# በአጥቢያ ቤ/ክ አመራር ሐዋርያትና ሽማግሌዎች በዋናነት አብረው ይሰሩ ነበር

- "አንዳንዶችም ከይሁዳ ወረዱና። እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም ብለው ወንድሞችን ያስተምሩ ነበር። በእነርሱና በጳውሎስ በበርናባስም መካከል ብዙ ጥልና ክርክር በሆነ ጊዜ፥ ስለዚህ ክርክር ጳውሎና በርናባስ ከእነርሱም አንዳንዶች ሌሎች ሰዎች ወደ ሐዋርያት ወደ ሽማግሌዎችም ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ዘንድ ተቈረጠ። ቤተ ክርስቲያኑም በመንገድ እየረዳቸው እነርሱ የአሕዛብን መመለስ እየተረኩ በፊንቄና በሰማርያ አለፉ፥ ወንድሞችንም ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙአቸው። ወደ ኢየሩሳሌምም በደረሱ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንና ሐዋርያት ሽማግሌዎችም ተቀበሉአቸው፥ እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ሁሉ አወሩ። ከፈሪሳውያን ወገን ግን ያመኑት አንዳንዶቹ ተነሥተው። ትገርዙአቸው ዘንድና የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁ ታዙአቸው ዘንድ ይገባል አሉ። **ሐዋርያትና ሽማግሌዎችም ስለዚህ ነገር ለመማከር ተሰበሰቡ።** ከብዙ ክርክርም በኋላ ጴጥሮስ ተነሥቶ እንዲህ አላቸው ወንድሞች ሆይ፥ አሕዛብ ከአፌ የወንጌልን ቃል ሰምተው ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር በመጀመሪያው ዘመን ከእናንተ እኔን እንደ መረጠኝ እናንተ ታውቃላችሁ።...ያን ጊዜ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ከቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ ጋር ከእነርሱ የተመረጡትን ሰዎች ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ወደ አንጾኪያ ይልኩ ዘንድ ፈቀዱ፤ እነርሱም በወንድሞች መካከል ዋናዎች ሆነው በርስያን የተባለው ይሁዳና ሲላስ ነበሩ።" ሐዋ 15፥1-6

# በአጥቢያ ቤ/ክ አመራር ሐዋርያትና ሽማግሌዎች በዋናነት አብረው ይሰሩ ነበር

- ”ጳውሎስ በእስያ እጅግ እንዳይቀመጥ ኤፌሶንን ይተው ዘንድ ቆርጦ ነበርና ቢቻለውም በዓለ ኀምሳን በኢየሩሳሌም ይውል ዘንድ ይቸኩል ነበርና። ከሚሊጢንም ወደ ኤፌሶን ልኮ የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች አስጠራቸው፤... በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።”ሐዋ 20፥16…28
- ”በነገውም ጳውሎስ ከእኛ ጋር ወደ ያዕቆብ ዘንድ ገባ ሽማግሌዎችም ሁሉ መጡ።”ሐዋ 21፥18
- ”እንግዲህ እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጕብኙት፤” 1ኛ ጴጥ 5፥1-2
- ”በእኛ ስለሚኖርና ከእኛ ጋር ለዘላለም ስለሚሆን እውነት፥ እኔ ሽማግሌው በእውነት ለምወዳቸውና እኔ ብቻ ሳልሆን እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ደግሞ ለሚወዱአቸው ለተመረጠች እመቤትና ለልጆችዋ”2ኛ ዮሐ 1፥1-2

# የሐዋርያት አገልግሎት

# ሐዋርያነት ፡ የስሙ ትርጓሜ

1. አፖስቶሎስ = በመለኮታዊ ስልጣን ለተለየ ተልእኮ ወይንም አገልግሎት የተላከ
2. ቃሉ ለመጀመሪያ በተግባር አገልግሎት ላይ ከዋለበት ክፍል በመነሳት
   - "...አስራ ሁለት መረጠ.. ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ስየማቸው" ሉቃ 6፥13
   - "ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው ፥ ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤" ማር 3፥14-15
3. የተላከው በላከው የተወከለ ነው (የተላከው የላከውን ሥራ ይሠራል)
   - አብ ወልድን - ወልድ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን - ወልድ/መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ሐዋርያትን ላከ (ሉቃ 6፥13፤ ዮሐ 13፥16፤ ዮሐ 12፥44-50፤ ሐዋ **13፥2**-4)

# በመጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያነት የተጠቀሱ

## 1. አሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት

- መለያቸው፡- በራሱ በክርስቶስ በቀጥታ መለየታቸው / መሰየማቸው (ሉቃ 6፥13)
- የትንሳኤው ምስክሮች መሆናቸው (ሐዋ 1፥3፣22- ፤ ሐዋ 10፡41)
- በላይኛይቱ መቅደስ ያላቸው ስፍራ/ መሠረት መሆናቸው (ራእ 21፥14)

## 2. ሌሎች ሐዋርያት

- ጳውሎስ (ሐዋ 14፥14, 14፤ 1ቆሮ 9፥1፤ገላ2:8)
- ባርናባስ (ሐዋ 4፥36፤ 11፥22-30፤ 14፥14, 14፤ 1ቆሮ 9፥6)
- ሲላስ / ሰልዋኖስ (ሐዋ 15:23፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 1፥1ና 2፥6)
- ሌሎችም

# ሐዋርያት ለሥራ እንዴት ይለዩ ነበረ?

**1) የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት አጠራር…**

” በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፥ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ። በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፥ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤እነርሱም፥…” ሉቃ. 6፥12-13

” እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፥ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ።” ዮሐ. 15፥16

# ሐዋርያት ለሥራ እንዴት ይለዩ ነበረ?

## 2) ሌሎች ሐዋርያት

*ከእርገቱ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ይጠሩ/ይሾሙ ነበር::*

”በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤...እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ **መንፈስ ቅዱስ። በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ።** በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው። እነርሱም **በመንፈስ ቅዱስ ተልከው** ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ፤...” ሐዋ. 13፥1-4

”**ሐዋርያት በርናባስና ጳውሎስ** ግን ይህን በሰሙ ጊዜ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቡ መካከል እየጮኹ ሮጡ፥ ” ሐዋ. 14፥14

# ሐዋርያት ለሥራ እንዴት ይለዩ ነበረ?

## የጾምና የፀሎት የአምልኮም ወሳኝ ሚና በሐዋርያት መጠራትና ለስራ መለየት ውስጥ

" በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፥ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ። በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፥ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤እነርሱም፥…" ሉቃ. 6፥12-13

" በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤…እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ **መንፈስ ቅዱስ። በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ።** በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው። እነርሱም **በመንፈስ ቅዱስ ተልከው** ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ፤…" ሐዋ. 13፥1-4

# ሐዋርያት ለሥራ እንዴት ይለዩ ነበረ?

*እግዚአብሔር* ***አስቀድሞ ለአገልግሎቱ በግል የጠራቸውን/ ያመለከታቸውን በመንፈስ ቅዱስ በኩል በቤተ ክርስቲያን(በቤተ ክርስቲያን ልዩ ጉባኤ) ይለያቸዋል***

"ለአባቶችም ወግ ከመጠን ይልቅ እየቀናሁ በወገኔ ዘንድ በዘመኔ ካሉት ብዙዎችን በአይሁድ ሥርዓት እበልጥ ነበር። ነገር ግን <u>በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ</u> በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም፥" ገላ. 1፥14-16

" እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ። ጌታ ሆይ፥ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው። ጌታም፦ ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው።...ጌታም፦ ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ፤ስለ ስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው <u>እኔ አመለክተዋለሁና</u> አለው።" ሐዋ. 9፥15

# የሐዋርያነት ምልክት / The Signs of an Apostle

## <u>እነዚህን ሰዎች እንዴት እናውቃቸዋለን?</u>

- መንፈስ ቅዱስ ለዩልኝ ሲል፣ ቤተክርስቲያን (በቤ/ክ ልዩ ጉባኤ) እውቅና ትሰጣቸዋለች፣ ሐዋ 13፥1-4
- ከቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የተላኩ ሲሆኑ ሐዋርያት ብለን እናውቃቸዋለን ሐዋ. 13፥1-4፣ ሐዋ 14፥14
- በፍሬአቸው እናውቃቸዋለን ሐዋ 11፥24-25፣..
- ከተሰየሙ በኋላ የሐዋርያነት ማህተም 1ኛቆሮ 9፥2
- በሐዋርያነት ምልክት እናውቃቸዋለን 2ኛ ቆሮ 12፥12

# የሐዋርያነት ምልክት

..እኔ ምንም ባልሆን እንኳ፥ ከዋነኞቹ ሐዋርያት ("super-apostles") በምንም አልጎድልምና። በእርግጥ የሐዋርያነት ምልክት (signs of an apostle) በመካከላችሁ በምልክትና በድንቅ ነገር በተአምራትም በሁሉ ትዕግሥት ተደረገ (performed among you with great perseverance by signs and wonders and powerful deeds)። እኔ ራሴ ካልከበድሁባችሁ ከዚህ በቀር፥ ከሌላ ቤተ ክርስቲያን ያነሳችሁበት በምን እኮ ነው? ይህን በደሌን ይቅር በሉልኝ። እነሆ፥ ወደ እናንተ እመጣ ዘንድ ስዘጋጅ ይህ ሦስተኛዬ ነው፤ አልከብድባችሁምም፥ እናንተን እንጂ ያላችሁን አልፈልግምና። ወላጆች ለልጆች እንጂ ልጆች ለወላጆች ገንዘብ ሊያከማቹ አይገባቸውምና። እኔ ግን ስለ ነፍሳችሁ በብዙ ደስታ ገንዘቤን እከፍላለሁ፥ ራሴን እንኳ እከፍላለሁ። ከመጠን ይልቅ ብወዳችሁ በዚህ ልክ ፍቅራችሁ የሚያንስ ነውን? ይሁን እንጂ እኔ አልከበድሁባችሁም፤ ነገር ግን ሸንጋይ ሆኜ በተንኰል ያዝኋችሁ። ...እንደ ገና ስመጣ በእናንተ ዘንድ አምላኬ እንዲያዋርደኝ (my God may humiliate me before you)፥ አስቀድመውም ኃጢአት ከሠሩትና ስላደረጉት ርኵሰትና ዝሙት መዳራትም ንስሐ ካልገቡት ወገን ስለ ብዙዎች ምናልባት አዝናለሁ ብዬ እፈራለሁ። 2ቆሮ 12:12-21

# በሐዋሪያት የምናያቸው መሠረታዊ ባሕሪያቶች

“የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን? እንደ እብድ ሰው እላለሁ፤ እኔ እበልጣለሁ፤ በድካም አብዝቼ፥ በመገረፍ አብዝቼ፥ በመታሰር አትርፌ፥ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ። አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ። ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርሁ፤ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተሰበረ፤ ሌሊትና ቀን በባሕር ውስጥ ኖርሁ።ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፥ በወንበዴዎች ፍርሃት፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት፥ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፥ በከተማ ፍርሃት፥ በምድረ በዳ ፍርሃት፥ በባሕር ፍርሃት፥ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፤ በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ። የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው። የሚደክም ማን ነው፥ እኔም አልደክምምን? የሚሰናከል ማን ነው፥ እኔም አልናደድምን?… በደማስቆ አርስጦስዮስ ከተባለ ንጉሥ በታች የሆነ የሕዝብ ገዥ ሊይዘኝ እየወደደ የደማስቆ ሰዎችን ከተማ ያስጠብቅ ነበር፥በቅጥሩም ባለ መስኮት በቅርጫት አወረዱኝና

ከእጁ አመለጥሁ።” (2ቆሮ 11:22-29)

”ሐዋርያት በርናባስና ጳውሎስ ግን ይህን በሰሙ ጊዜ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቡ መካከል እየጮኹ ሮጡ፥…” (ሐዋ 14:14)

# በሐዋሪያት የምናያቸው መሠረታዊ ባሕሪያቶች

- “ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን፤ በብዙ መጽናት፥ በመከራ፥ በችግር፥ በጭንቀት፥ በመገረፍ፥ በወኅኒ፥ በሁከት፥ በድካም፥ እንቅልፍ በማጣት፥በመጦም፥ በንጽህና፥ በእውቀት፥ በትዕግሥት፥ በቸርነት፥ በመንፈስ ቅዱስ፥ ግብዝነት በሌለው ፍቅር፥ በእውነት ቃል፥ በእግዚአብሔር ኃይል፥ ለቀኝና ለግራ በሚሆን በጽድቅ የጦር ዕቃ፥ በክብርና በውርደት፥ በክፉ ወሬና በመልካም ወሬ ራሳችንን እናማጥናለን፤ አሳቾች ስንባል እውነተኞች ነን፤ ያልታወቁ ስንባል የታወቅን ነን፤ የምንሞት ስንመስል እነሆ ሕያዋን ነን፤ የተቀጣን ስንሆን አንገደልም፤ ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፤ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለ ጠጎች እናደርጋለን፤ አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው።” (2ቆሮ 6:4-10)
- ሐዋ 14:14 ሐዋርያት በርናባስና ጳውሎስ ግን ይህን በሰሙ ጊዜ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቡ መካከል እየጮኹ ሮጡ፥
- 2ቆሮ 11:28-”...የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው።”
- 1ቆሮ 4:9-13 “ለዓለም ለመላእክትም ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናልና፤ እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች እንዳደረገን ይመስለኛልና።”
- 2ኛ ተሰ 3፣3 “በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጌታ ቃል እንዲሮጥ በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን እንዲከበር፥ እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን ከዓመፀኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንድንድን ስለ እኛ ጸልዩ።”

# በሐዋሪያት የምናያቸው መሠረታዊ ባሕሪያቶች

አይነተኛ መለያ (ፓተርን)/ በሐዋርያዊ ሰው ላይ በተደጋጋሚና በቋሚነት የሚታይ አይነተኛ ባሕርይ ምን ይመስል ነበረ?

- በመከራ መጽናታቸው ("በሁሉ ትግስት" ማድረጋቸው/ ) (2ቆሮ 12:12-21)
- በድንቅና በተአምራት የተለየ ጸጋ በምልክትም (2ቆሮ 12:12-21)
- ፍጹም የሆነ የሕይወት መሰጠት ያላቸው፣ ገንዘባቸውን፣ ነፍሳቸውን ለሚያገለግሏቸው የሰጡ (ፊል 2፥17)
- መንፈሳዊ ስልጣናቸው (2ኛ ቆሮ 10፥8)
- ከአጥቢያ ቤ/ክ ያለፈ እይታቸው፡ ሃላፊነት መውሰዳቸው፡ (ቆላ 2: 1-2)
- በጊዜ የታዩና የተመሰከረላቸው መሆናቸው (2ኛ ጴጥ. 3፥15/ ሐዋ. 20፥18-19)
- ሐዋሪያትን ልዩ ከሚያደርጋቸው ነገር አንዱ ለዘመናት ተሰውሮ የነውበሩ እውነቶችን መግለጥ መቻላቸው ነው (ኤፌ 3፡1-6 )

# የሐዋሪያት አገልግሎትና ሃላፊነታቸው

<u>ቤተክርስቲያንን መትከል፡ መልክ መስያዝና የሚገባውን ነገር መደንገግ</u>

”በኢየሩሳሌምም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው። እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤” (ሐዋ 8:14-17)

”ያላዘዝናቸው ሰዎች ከእኛ ወጥተው ትገረዙ ዘንድና ሕግን ትጠብቁ ዘንድ ይገባችኋል ብለው ልባችሁን እያወኩ በቃል እንዳናወጡአችሁ ስለ ሰማን፥...ለጣዖት ከተሠዋ፥ ከደምም፥ ከታነቀም፥ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና፤ ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ። ጤና ይስጣችሁ።"(ሐዋ 15:24, 28-29)”

"ብቻ ለእያንዳንዱ እግዚአብሔር እንደ ከፈለለት እያንዳንዱም እግዚአብሔር እንደ ጠራው እንዲሁ ይመላለስ። እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እደነግጋለሁ።" (1ቆሮ 7:17)

"ማንም የራበው ቢኖር ለፍርድ እንዳትሰበሰቡ በቤቱ ይብላ። የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ።" (1ቆሮ 11:34)

"እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን። ይህም ቃል ሕዝብን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፤ እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን ፊልጶስንም ጵሮኮሮስንም ኒቃሮናንም ጢሞናንም ጳርሜናንም ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን የአንጾኪያውን ኒቆላዎስንም መረጡ።በሐዋርያትም ፊት አቆሙአቸው፥ ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው።"ሐዋ 6:4-6

# የሐዋሪያት አገልግሎትና ሃላፊነታቸው

## ለዘመናት የተሰወረን ሚስጥር መግለጥ የሐዋሪያት ልዩ አገልግሎት ነበር

- “ይህም፥ አሕዛብ አብረው እንዲወርሱ፥ በአንድ አካልም አብረው እንዲሆኑ፥ በወንጌልም መስበክ በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነ የተስፋ ቃል አብረው እንዲካፈሉ፥ ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለነቢያት በመንፈስ አሁን እንደ ተገለጠ በሌሎቹ ትውልዶች ዘንድ ለሰው ልጆች አልታወቀም። እንደ ኃይሉ ሥራ እንደ ተሰጠኝም እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ መጠንየወንጌል አገልጋይ ሆንሁለት። ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለ ጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ፥ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለኔ ተሰጠ፤” ( ኤፌ 3:5-9 )
- “እኔም ለዚህ ነገር አዋጅ ነጋሪና ሐዋርያ በእምነትና በእውነትም የአሕዛብ አስተማሪ ለመሆን ተሾምሁ፤ እውነት እናገራለሁ፤ አልዋሽም።” (1ኛ ጢሞቴዎስ 2:7)
- “ስለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ። ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው፥ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል።...” (ቆላስ. 1:25)
- “ለተገረዙት ሐዋርያ እንዲሆን ለጴጥሮስ የሠራለት፥ ለእኔ ደግሞ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንድሆን ሠርቶአልና።” (ገላ 2፡8)

# ሐዋሪያት በሌሎቹ አገልግሎቶች ውስጥ

## ሐዋሪያት ባሉበት አጥቢያ በሽማግሌነት አገልግለዋል

- “እንግዲህ እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤” ጴጥሮስ በሽማግሌነት (1ጴጥ 5፡1) (amplified) ([1] *The elderly elder* [of the church addresses this letter] to the beloved (esteemed) Gaius, whom I truly love. (the Amplified Bible)
- “ሽማግሌው በእውነት እኔ ለምወደው ለተወደደው ለጋይዮስ።” (ዮሐንስ በሽማግሌነት (1ዮሐ ---፣ 3ዩሐ:1 / በኤፌሶን) (ዮሐንስ በነቢይነት)
- ”እኔም ለዚህ ነገር አዋጅ ነጋሪና ሐዋርያ በእምነትና በእውነትም የአሕዛብ አስተማሪ ለመሆን ተሾምሁ፤ እውነት እናገራለሁ፤ አልዋሽም።” ጳውሎስ በወንጌላዊነት በአስተማሪነት (1ጢሞ 2:7)

# የእረኝነት አገልግሎት

# የእረኝነት አገልግሎት ምንድን ነው?

**Pas'-ter (ro`eh; poimen)**

የበጎች መጋቢ (feeder of the sheep) ወይንም ረዳት (a helper) ማለት ነው።

በዚሁ ትርጉሙ (በተውላጠ ስም / Noun form) በአዲስ ኪዳን ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ጋር በተያያዘ በኤፌሶን 4፡11 ላይ ብቻ ተጠቅሷል።

በአንጻሩ እረኛ፣ መጋቢ ፣ ሽማግሌ፣ ጳጳስ፣ ኤጲስ ቆጶስ የሚሉት ቃሎች በሙሉ **በተወራራሽነት አንዱን ሰው ወይንም አገልግሎት/ሥራ ለመግለጽ ተጠቅሟል።**

ሐዋ 20:17,28 ፤ ቲቶ 1:5,7፤ 1ጴጥ 5:1-4፤ ኤፌ 4፡11፤ 1ኛ ጢሞ 3:1

# የእረኝነት አገልግሎት ምንድን ነው?

እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም <u>እረኞችና</u> አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ( ኤፌ 4 :11 )

Eph 4 <u>(KJV with Strong's Numbers)</u>

Eph 4: 11 And<2532> | he<<u>846</u>> | gave<<u>1325</u>> | some<3588>, | apostles<<u>3303</u>><<u>652</u>>; | and<1161> | some<3588>, | prophets<<u>4396</u>>; | and<1161> | some<3588>, | evangelists<<u>2099</u>>; | and<1161> | some<3588>, | **pastors<<u>4166</u>>** | and<2532> | teachers<<u>1320</u>>;

# የእረኝነት አገልግሎት ምንድን ነው?

"ከሚሊጢንም ወደ ኤፌሶን ልኮ የቤተክርስቲያንን **ሽማግሌዎች** አስጠራቸው፤.... 28 በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን **ትጠብቁአት ዘንድ** መንፈስ ቅዱስ እናንተን **ጳጳሳት** አድርጎ ለሾመባት **ለመንጋው** ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።" (ሐዋ 20:17, 28)

**17** And<3588><1161> | from<575> | Miletus<3588><3399> | he sent<3992> | to<1519> | Ephesus<2181>, | and called<3333> | **the elders<4245>** | of the church<3588><1577>....

**28** Take heed therefore unto yourselves, and to all the flock, over the which the Holy Ghost hath made you overseers, to feed the church of God, which he hath purchased with his own blood.

Acts 20: 28 Take heed<3588><3588><4337> | therefore<3767> | unto yourselves<1438>, | and<2532> | to all<3956> | the **flock<3588><4168>,** | over<1722> | the which<3739> | the Holy<40> | Ghost<3588><4151> | hath made<5087> | you<5209> | **overseers<1985>,** | **to feed<4165>** | the church<3588><1577> | of God<3588><2316>, | which<3739> | he hath purchased<4046> | with<1223> | his own<2398> | blood<129>.

# የእረኝነት አገልግሎት ምንድን ነው?

ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም፥ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፥ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ፤ የማይነቀፍና የአንዲት ሚስት ባል የሚሆን፥ የሚያምኑም ልጆች ያሉት፥ ስለ መዳራትም ወይም ስለ አለመታዘዝ የማይከሰስ ማንም ቢኖር፥ ሹመው። ኤጲስ ቆጶስ፥ እንደ እግዚአብሔር መጋቢ፥ የማይነቀፍ ሊሆን ይገባዋልና፤ የማይኮራ፥ የማይቆጣ፥ የማይሰክር፥ የማይጨቃጨቅ፥ ነውረኛ ረብ የማይወድ፥ ነገር ግን እንግዳ ተቀባይ፥ በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ፥ ጠንቃቃ፥ ጻድቅ፥ ቅዱስ፥ ራሱን የሚገዛ ይሁን፤ (ቲቶ 1:5-7)

Titus 1 (KJV with Strong's Numbers)
Titus 1: 5 For this<5127> | cause<5484> | left I<2641> | thee<4571> | in<1722> | Crete<2914>, | that<2443> | thou shouldest set in order<1930> | the things<3588> | that are wanting<3007>, | and<2532> | ordain<2525> | elders<4245> | in every<2596> | city<4172>, | as<5613> | I<1473> | had appointed<1299> | thee<4671>:

7 For<1063> | a bishop<3588><1985> | must<1163> | be<1511> | blameless<410>, | as<5613> | the steward<3623> | of God<2316>; | not<3361> | selfwilled<829>, | not<3361> | soon angry<3711>, | not<3361> | given to wine<3943>, | no<3361> | striker<4131>, | not<3361> | given to filthy lucre<146>;

63

# የእረኝነት አገልግሎት ምንድን ነው?

1ኛ ጴጥ 5:1-4 እንግዲህ እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ (fellow elder, niv & amp) የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ (shepherd, niv; feed, kjv)፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን (not greedy for money, niv) ጐብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ። (1ኛ ጴጥ 5:1-4)

1Pet 5: 1 The elders<3588><3588><3588><4245> | which<3588> | are among<1722> | you<5213> | I exhort<3870>, | who<3588> | am also an elder<4850>, | and<2532> | a witness<3144> | of the sufferings<3804> | of Christ<3588><5547>, | and also<2532> | a partaker<2844> | of the glory<1391> | that shall<3195> | be revealed<601>:

4 And when<3588><2532> | the chief Shepherd<3588><750> | shall appear<5319>, | ye shall receive<2865> | a crown<4735> | of glory<3588><1391> | that fadeth not away<262>.

# ሁሉም ቃሎች አንዱን አገልግሎት/ ሰው ያሳያሉ!

| | ሽማግሌ<br>Elder or Presbyter | ጳጳስ/ኤጲስ ቆጶስ<br>Overseer or bishop | እረኛ<br>Shepherd or pastor | መጋቢ<br>Steward |
|---|---|---|---|---|
| የግሪክ ቃል → | PresbuTeros | Episcopos | Poimen (4166) | Oikonomo |
| ትኩረቱ/ የሚያሳየው → | በቆይታ የተገኘን ልምድ፣ ጥበብ | ከፍተኛውን የመንፈሳዊ ሥልጣን፣ የበላይ ጥበቃን | ሌሎችን መጠበቅ፣ እንክብካቤን፣ በፍቅር ዋጋ መክፈልን ጨምሮ | ከፍ ላለ ዋጋ መታመንን |
| **ኤፌ 4:11** | | | (4166) | |
| **ሐዋ 20:17,28 *** | (4245) | (1985) | (4168) (4165) | |
| **ቲቶ 1:5,7** | (4245) | (1985) | | (3623) |
| **1ጴጥ 5:1-4** | (4245) | | (4168) | |

# እረኞች/ኤጲስ ቆጶሳት/መጋቢዎች/ ሽማግሌዎች

# በማን እንዴት ይሾሙ ነበር?

አስቀድሞ በጌታ በራሱ / በመንፈስ ቅዱስ ይጠራሉ ይሾማሉ

- ሐዋ. 20:28 "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ **ለሾመባት** ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።"
- ሉቃስ 12:42 "ጌታም አለ። እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ ሰዎቹ ላይ **የሚሾመው** ታማኝና ልባም መጋቢ ማን ነው?"

# በማን እንዴት ይሾሙ ነበር?

**ሽማግሌዎች የሚሾሙት (appointed የሚሆኑት, amp) በሐዋርያትና ከሐዋርያት ሽማግሌ ለመሾም ቀጥተኛ ሃላፊነት በተሰጣቸው አጋር አገልጋዮች ነበር**

- ጳውሎስና በርናባስ በየቤተክርስቲያኑ ሽማግሌዎችን ሾሙ (ordain አደረጉ)

ሐዋ 14:23 በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው (appointed and ordained, amp; appointed, niv) በኋላ ጦመውም ከጸለዩ በኋላ፥ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡአቸው።

- ጳውሎስ ለቲቶ ሽማግሌዎችን በየከተማው እንዲሾም (ordain እንዲያደርግ) አዘዘው።

ቲቶ 1:5 "ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም፥ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፥ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ፤"

- ጳውሎስ ጢሞቲዎስን ሽማግሌዎች/ለመሾም እንዳይቸኩል አሳሰበው።

1ኛ ጢሞ 5:22 "በማንም ላይ ፈጥነህ እጆችህን አትጫን፥ በሌሎችም ኃጢአት አትተባበር፤ ራስህን በንጽህና ጠብቅ

# ሹመታቸው/አገልግሎታቸው እስከመቼ ነው?

**"ሰጠ/gave"** (ኤፌ 4 : 11) የእግዚአብሄር ድርሻ /መምረጥና መጥራት

**"ሾሙ/ordain"** (ሐዋ 14:23 & ቲቶ 1:5) የቤተክርስቲያንን እውቅና መስጠት

"ordain" ማለት እስከመጨረሻው / በዘላቂነት አንድ የሃላፊነት ስፍራ ላይ ማስቀመጥ ማለት ነው (dictionary meaning፡ to place down permanently; to designate)

**ስለዚህ የሽማግሌዎች/የእረኝነት አገልግሎት በጉባኤ ምርጫ/ የእጅ ብልጫ የሚመረጡና የሚወርዱ አልነበሩም።**

# ሽማግሌዎች አገልግሎታቸው የወል ነው !

የሽማግሌዎች አገልግሎት የተጠቀሰው -ዎች እየተባለ (በግሪኩ “Presbuterion” በሚለው ቃል) ብዛትንና እኩልነትን በሚያሳይ መልኩ ነው።

- ሐዋ 20:17,28 ከሚሊጢንም ወደ ኤፌሶን ልኮ የቤተክርስቲያንን ሽማግሌዎች አስጠራቸው፤
- ቲቶ 1:5,7 ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም፥ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፥ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ
- ሐዋ 15:2-4,6 …ስለዚህ ክርክር ጳውሎና በርናባስ ከእነርሱም አንዳንዶች ሌሎች ሰዎች ወደ ሐዋርያት ወደ ሽማግሌዎችም ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ዘንድ ተቈረጠ።
- ሐዋ 11:30 እንዲህም ደግሞ አደረጉ፥ በበርናባስና በሳውልም እጅ ወደ ሽማግሌዎቹ ሰደዱት።
- ያዕ 5:14 ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽምግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት።

**በመጽሃፍ ቅዱስ የአንድ ሰው ብቸኛ (solo) የቤ/ክ አመራርን አናይም**

# የሸማግሌዎች ሥራ ምንድን ነበረ?

# የሽማግሌነት መለያዎች ምንድን ናቸው?

# የመወያያ ጥያቄዎች 2

- በኤፌ. 4:11-13 መሠረት አምስቱ አገልግሎቶች በቤተክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ ምን ምን ሚና እንዳላቸውና እንዴትም ቅዱሳንን ወደክርስቶስ ሙላት ለማድረስ እንደሚያገለግሉ እያነሳህ ተወያይ። አስፈላጊነታቸው  እስከመቼ ድረስ ነው? ለዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያንስ？
- መጽሐፍ ቅዱስ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች/ እረኞች/ኤጲስ ቆጶሳት/መጋቢዎች የሚሉትን ሃላፊነቶች በተወራራሽነት ነው የተጠቀመባቸው። ይህ ምን ትርጉም ይሰጠናል?
- ሽማግሌዎች በአንድ አጥቢያ ቁጥራቸው የተጠቀሰው በወል ነው። ከዚህ ምን እንማራለን？

# የመወያያ ጥያቄዎች 2

- ከሐዋ 13:1,2 እና ሐዋ 20:28፤ ሐዋ 14:23፤ እና ኤፌ 4:8,11 አንጻር የቤተክርስቲያን መሪዎች (አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች) የሚጠሩት የሚለዩትና የሚሾሙት እንዴት ነበር? የአማኞች ድርሻስ ምን ነበር?
- በቤተክርስቲያን አመራር የሐዋርያት ድርሻ ምንድር ነበር？

"በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ሐዋርያት በአጥቢያ ቤተክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ ከሽማግሌዎች ጋር በጣምራ እንዴት ያገለግሉ እንደነበረ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌ የሆኑ ክፍሎችን በመመልከት ተወያይ::"

- መጽሐፍ ቅዱስ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የሥራ ድርሻ ምንድን ነው ይላል?